Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

MCPS Document 335-9C
ጃኑዋሪ 2023

# የቅድመ-መዋእለ ህፃናት/ሄድ ስታርት ፕሮግራሞች
# የትምህርት ዓመት 2023–2024 የሠነዶች ዝርዝር

**Division of Early Childhood, Title I Programs and Recovery Funds**
Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Room 143, Rockville, Maryland 20852

ለቅድመ ሙአለህፃናት/ሄድስታርት ልጆች፣ የአካል ስንክልና ያላቸውን ህጻናት ጨምሮ ያለቀጠሮ በአካል ማመልከቻ ፎርም ይዘው ለመቅረብ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ9:00 a.m. እስከ 4:00 p.m. በ Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Rockville, Maryland, 20852 ተቀባይነት ይኖራቸዋል። በዚህ ቅጽ ላይ ስለተጠቀሱት ሠነዶች ጥያቄዎች ካሉዎት እና/ወይም የእርስዎን የተለየ ሁኔታ በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ በስልክ ቁጥር:- 240-740-4530 ይደውሉ ወይም ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ www.montgomeryschoolsmd.org።

**ማመልከቻውን ለመሙላት፣ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሠነዶች ማቅረብ አለብዎት።**

የሚከተለውን ዝርዝር በመመሪያነት ይጠቀሙ:-

❑ 1. የተማሪ የእድሜ ማረጋገጫ እና መታወቂያ— ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች/ዶኩመንቶች አንዱን ያቅርቡ።
  - የልደት ሠርተፊኬት
  - ፓስፖርት
  - የሃኪም ሠርተፊኬት
  - የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን ሠርተፊኬት
  - የሆስፒታል ሠርተፊኬት
  - የሠነድ ማረጋገጫ/ኖቶራይዝ የተደረገ የወላጅ ቃለመኃላ/affidavit
  - የልደት ምዝገባ ሠርተፊኬት፣ ወይም
  - ሌሎች ህጋዊ የሆኑ ወይም የሠነድ ማረጋገጫ/ኖቶራይዝ የተደረጉ የልጆች መታወቂያ እና የልደት ቀን ማረጋገጫ።

❑ 2. ተማሪው(ዋ)ን ወደ ትምህርት ቤት የሚያስገባው/የምታስገባው ሰው መታወቂያ እና ከተማሪው(ዋ) ጋር ያለ ግንኙነት—
  ፎተግራፍ ያለበት የማንነት መታወቂያ ምሳሌዎች የሚያካትተው—እባክዎ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች/ዶኩመንቶች አንዱን ያቅርቡ።
  - የመንጃ ፈቃድ
  - ፓስፖርት
  - ከሞተር ተሽከርካሪዎች አስተዳደር የተሰጠ መታወቂያ ካርድ/Motor Vehicle Administration ID Card
  - ሌላ ______________________________

  ከተማሪ ጋር ያለ ግንኙነትን በሚመለከት የሚካተቱ ምሣሌዎች—ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች/ዶኩመንቶች አንዱን ያቅርቡ።
  - የልጅ የልደት ሠርተፊኬት
  - የፍርድ ቤት ትዕዛዝ
  - ለመለያየት የተደረገ ስምምነት ወይም የፍቺ ሠነድ፣ ወይም
  - ሌላ ህጋዊ መታወቂያ ______________________________

❑ 3. የቤተሰብ የገቢ ማረጋገጫ (ጎልማሳ የቤተሰብ አባላት በሙሉ)— ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች/ዶኩመንቶች እርስዎን የሚመለከቱ ሠነዶችን በሙሉ ያቅርቡ።
  ምሳሌዎች የሚያካትቱት:-
  - Tax return for 2022—1040, W2s, Schedule C/1099
  - ሦስት ወቅታዊ የደሞዝ (ዌጅ) ክፍያ ሠነዶች/pay stubs
  - የሥራ ቅጥር ደብዳቤዎች
  - ስለ ልጅ ማሳደጊያ ድጋፍ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ደብዳቤ
  - የዶላር መጠን የሚያሳይ የፋይናንስ እርዳታ ደብዳቤ
  - ጊዜያዊ የገንዘብ ድጎማ (TCA)
  - የኪራይ ገቢ ደብዳቤዎች
  - የሥራ አጥነት፣ የአካል ስንክልና ገቢ፣ ወዘተ

❑ 4. ወቅታዊ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪነት ማስረጃ
  - የግል መኖሪያ ቤት ባለቤት ከሆኑ—ተቀባይነት የሚኖረው ወቅታዊ የንብረት ታክስ ሠነድ ነው
  - ቤትዎን የተከራዩ ከሆነ—ተቀባይነት የሚኖረው ወቅታዊ ሊዝ ነው* (የሚመለከትዎ ከሆነ፣ የ HOC፣ የኪራይ ወይም ዩቲሊቲ ድጋፍ የሚሰጥ ካለ አባሪ ይደረግ)።
    *ኦርጅናል የሊዝ ስምምነት ያበቃለት ከሆነ፣ የሊዙን ቅጂ እና ወቅታዊ ዩቲሊቲ ቢል ያቅርቡ
  - በ MCPS ትምህርት ቤት አካባቢ በህጋዊነት ኗሪ ከሆነ/ች የቤት ባለቤት ጋር ወይም ከተከራይ ጋር በደባልነት የሚኖሩ ከሆነ—
  - የሠነድ ማረጋገጫ ማህተም/ኖቶራይዝ የተደረገ MCPS Form 335-74፣የመኖሪያ ቤት ደባልነት መግለጫ/Shared Housing Disclosure በአግባብ ተሞልቶ መቅረብ አለበት፣ የቤት ባለቤትነት ወቅታዊ የንብረት ታክስ ሠነድ/ቢል ቅጂ፣ ወይም የመኖሪያ ቤት ኪራይ-ሊዝ ቅጂ (ኦርጅናል የኪራይ ውል/ሊዝ ጊዜው ያለፈበት ከሆነ፣ የሊዝ ውል ቅጂ እና ዩቲሊቲ ክፍያ ሠነድ-ቢል)፣ ተፈርሞበት ኖቶራይዝ የተደረገ የ MCPS Form 335-74፣ እና ወላጅ/ሞግዚት ወይም ብቁነት ያለው/ያላት ተማሪ በተገለጸው አድራሻ ነዋሪ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ሦስት ዶኩሜንቶችን ማቅረብ። MCPS Form 335-74 ተሞልቶ እና ተፈርሞበት ህጋዊ ሰነድ መሆኑን ሲፈረም የተረጋገጠ/notarized ከሆነ አድራሻ ለማረጋገጥ ከሦስቱ አስፈላጊ ማረጋገጫዎች አንዱ ሆኖ ሊቆጠር ይችላል።

❑ 5 እባክዎ የእርስዎን ሁኔታ የሚመለከት ከሆነ የሚከተሉትን ሠነዶች/ዶኩመንቶች ያቅርቡ:-
- የህጻኑ(ኗ) የህክምና ኢንሹራንስ ካርድ (ካለ)
- WIC Folder-ፋይል (የሚመለከትዎት ከሆነ)
- የምግብ ድጎማ ፕሮግራም/Food Supplement Program (FSP) ደብዳቤ (ቀደም ሲል ፉድ ስታምፕስ ይባል ነበር) (የሚመለከትዎ ከሆነ)
- የልጅ ነጻ ትምህርት ቫውቸር/Child Care Scholarship Voucher (የሚመለከትዎ ከሆነ)
- የልጅ እንክብካቤ ሰጪ ስም እና አድራሻ (የሚመለከትዎ ከሆነ)
- በልጁ/በልጅቱ ግላዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ፕሮግራም/Individualized Education Program (IEP)፣ የሞግዚትነት/በማደጎ የማሳደግ የተንከባካቢነት ማረጋገጫ (የሚመለከትዎ ከሆነ)